

ጰ34-2ጸ

# ከመጥፎ ልምምድ እንሽሽ

**“የብልጽግና ወንጌል” (Prosperity Gospel)**

የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎች፥ ሰዎች ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለጌታ እንዲሰጡ ከመስበክና ከማስተማር ይልቅ፥ በብልጽግና ትምህርት (Prosperity Gospel) የአዳማጮቻቸውን ልብ ሞቅ ማድረግ ደስ ይላቸዋል።

1) “መቶ እጥፍ ይቀበላል”

የብልጽግና ትምህርት አክራሪዎች ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ጥቅስ “ስለ እኔና ስለ ወንጌል ብሎ ቤትን ወይንም ወንድሞችን ወይንም እህቶችን ወይንም እናትን ወይንም አባትን ወይንም ልጆችን ወይንም ርስትን የሚተው ሰው ይበልጥ ያገኛል፤ በመቶ እጥፍ ይቀበላል” (ማር. 10፥29፥30) የሚለውን ነው። የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች ይህን ቃል በቃል ይወስዱታል። የሚጠቀሙበትም “ይቀበላል” የሚለው ብቻ ቆርጠው በመውሰድ ነው። “እምነት ካለን አሥር ብር ሰጥተን እንደ ሆነ አንድ ሺ ብር ለመቀበል መብታችን ነው” ይላሉ። “በዚህ ዘመን” የሚለውን ቃል አለአግባብ በመጠቀም ደግሞ ይሄ መቶ እጥፍ ዋጋ የምንቀበለው በሰማይ ሳይሆን አሁኑኑ ነው ይላሉ። እነዚህ የብልጽግና ትምህርት አክራሪዎች የዘነጉት ነገር ቢኖር “መቶ እጥፍ” ትቀበላላችሁ ያለው ገንዘብ ወይንም ሀብት ብቻ አለመሆኑን ነው፤ “ወንድሞች፣ እህቶችን፣ እናትንስ” አያጠቃልልም” ማንም መቶ ወንድሞች፣ መቶ እህቶች ወይንም መቶ እናቶች ስለማይኖረው ኢየሱስ የተናገረው ተስፋ ቃል በቃል የሚተረጎም አለመሆኑን የዘነጉት ይመስላል። ኢየሱስ ይህን ተስፋ የሰጠው እርሱን ለመከተል ሲሉ ሁሉን የተዉትን ነው። አብዛኛዎች እነዚህ የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች የሚሰብኩላቸው ይህንን ነጥብ ያሟሉ አይደሉም። ኢየሱስ ይህን የተናገረው ሰው ኢየሱስን በመከተሉ የሚያገኘው ብልጽግና ምን ያህል ትልቅ እንደ ሆነ ለመግለጽ ሳይሆን ብልጽግና ላይ ዓይኑን የሚያተኩር ሰው የሚያጋ ጥመውን ወጥመድ ለመግለጽ መሆኑን የብልጽግና ትምህርት አክራሪዎች የተረዱት አይመስ ለንም።

2) የትምህርቱ መሠረት ከየት የመጣ ነው?

እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ የሚል ቃል ኪዳን ገብቶለታል። “ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ታዘዝ ከዚህ የሚከተሉት በረከቶች ሁሉ ባለቤት ትሆናለህ። እግዚአብሔር ከተሞችህንና እርሻዎችህን ይባርካል። እግዚአብሔር ብዙ ልጆችን እጅግ የተትረፈረፈ የእርሻ ሰብል ብዙ የቀንድ ከብት የበግንና የፍየልን መንጋ በመስጠት ይባርክሃል። እግዚአብሔር የእህል ሰብልህንና ከእርሱ የምትሠራውን ምግብ ሁሉ ይባርካል። እግዚአብሔር በቤትህ ሳለህና ወደ ሥራ ስትወጣ ይባርክሃል” ይላል (ዘዳ. 28፥2-6)። ይህንን የአብርሃምን ተስፋ በመጥቀስ አማኝ ከድህነትና ከበሽታ ነጻ ነው ይላሉ። ይህን የብሉይ ኪዳን ተስፋ ከአዲስ ኪዳን ጋር የሚያያይዙበት ጥቅስ አላቸው። “በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጻፈ፥ ክርስቶስ

ስለ እኛ እንደ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን። ይህም የሆነው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው በረከት በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለአረማውያን እንዲደርስና እግዚአብሔር እሰጣችኋለሁ ያለውን መንፈስ ቅዱስን በእምነት እንድንቀበል ነው። እንግዲህ የክርስቶስ ከሆና ችሁ የአብርሃም ዘር ናችሁ፤ በተስፋውም ቃል መሠረት ወራሾች ናቸሁ (ገላት 3፥13-14፥29) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ ነው። በዚህ ጥቅስ መሠረት እኛ የአብርሃም ልጆች ከሆንን እግዚአብሔር የገባለት የብልጽግና ተስፋ ሁሉ የእኛ ነው የሚል ነው። በመሠረቱ ጳውሎስ በገላትያን ላይ የገለጸው ተስፋ ምድራዊ ብልጽግና ሳይሆን በእምነት ድህንነትን እንደሚያገኙና መንፈስ ቅዱስን እንደሚቀበሉ ነው። ጳውሎስ ስለ ስጋ ጤንነትና ስለ ምድራዊ ብልጽግና በገላትያን መልዕክቱ ምንም አልጠቀሰም። የጳውሎስን ደብዳቤ ገንጥለው ለዓላማቸው እንዲመች ብቻ ተጠቅመውበት ነው።

3) "እንድትበለጽግ እመኛለሁ"

የብልጽግና ትምህርት አክራሪዎች ለዓላማቸው እንዲመቻቸው በጣም የሚጠቀሙበት ጥቅስ "በነፍስህ ደህና እንደሆንህ አውቃለሁ፤ እንዲሁም ኑሮህ ሁሉ እንዲሳካልህና ጤንነትም እንዲኖርህ እጸልይልሃለሁ" (3ኛ ዮሐ. 2) የሚለውን ጥቅስ ነው። የዚህ ጥቅስ ትርጉም ብዙዎች የገባቸው አይመስለንም። እዚህ ላይ ጳውሎስ ለጋይዮስ የሚመኘውን ምኞቱን ብቻ ነው የገለጸው እንጂ ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ የተስፋ ቃል አልነበረም። ብልጽግና በብሉይ ኪዳን የእግዚአ ብሔርን ሕግ ለሚታዘዙ የሚሰጥ በርከት ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ተመሳሳይ ቃል በብዙ ቦታ ተጽፎ ስለአላገኙ የብልጽግና ትምህርት አክራሪዎች ለትምህርታቸው ይመቻል ሲሉ 3ኛ ዮሐንስ ቁጥር 2ን አብዝተው ይጠቅሱታል። ይጥቀሱት እንጂ እነርሱ ከሚሉት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

4) በዘራነው መጠን እናጭዳለን

"ጥቂት የዘራ ጥቂት መከር ይሰበስባል፤ ብዙ የዘራ ብዙ መከር ይሰበስባል" (2ኛ ቆር 9፥6) የሚለውን የጳውሎስን ትምህርት የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች ይጠቅሱታል። ይህንን ቃል ያለአግባቡ በመጠቀም በአቋራጭ ሀብታም ወይንም ባለጸጋ ለመሆን የሚችሉበት መንገድ እንደ ሆነ አድርገው ይወስዱታል። አንድ ጊዜ በዚህ ትምህርት የተቀሰቀሰ አንድ ሰው ቤቱን ሸጦ "ለብልጽግና ትምህርት" ሰባኪዎች ሰጠ። የሰጠበት ዋናው ምክንያት ለመስጠት ልቡን ተነክቶ ሳይሆን ቀድሞ ከነበረው ቤት ይልቅ ብዙ ዋጋ የሚያውጣ ትልቅ ቤት አገኛለሁ ብሎ በማሰብ ነበር። የሚያሳዝነው ነገር ግን የብልጽግና ትምህርት ሰባኪው እንደ ተናገረው ትልቅ ቤት በማግ ኘት ፈንታ ቀድሞ የነበረውንም ቤቱን አጥቶ ባዶ እጁን ቀረ። በዚህ ዓይነት በጡረታ አበላቸው ብቻ የሚተዳደሩትን ሽማግሌዎችንና አሮጊቶችን ከመስመር በወጣ ትምህርታቸው የሚገፉ የብልጽግና ትምህርት አስተማሪዎች አሉ።

ሐ) "እርግጠኛ የእምነት ኑዛዜ" (Positive Confession)

የዚህ "የእርግጠኛ የእምነት ኑዛዜ" ትምህርት ሰባኪዎች የሚጠቀሙበት "በእውነት እላችኋለሁ ማንም ሰው በልቡ ሳይጠራጠር የሚፈልገው ነገር እንደሚፈጸምለት አምኖ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነሥተህ ወደ ባህር ተወርወር ቢል ይሆንለታል። ስለዚህ በጸሎት ማናቸውንም ነገር ብትለምኑ እንደሚፈጸምላችሁ እመኑ የምትለምኑትም ሁሉ ይሰጣችኋል" (ማር. 11፥23-24) የሚለው ጥቅስ ነው። ከጌታ ለመቀበል በእምነት መጠየቅ እንዳለብን ግልጽ ነው። ይሄ ምንም

ስህተት የለውም። ይሁን እንጂ አንዳንዶች ይህንን ቃል ከመስመር በወጣ መንገድ ይጠቀሙ በታል። የዚህ ትምህርት ተከታይ የነበረች ሴት ይህንን ጥቅስ በመጠቀም ደስ የሚላትን ወንድ አይታ "በኢየሱስ ስም አንተ ሰው የእኔ ባል እንድትሆን በእምነት እጠይቃለሁ አንተ ወጣት እምቢ ማለት ምንም ሳልጣን የለህም" ስትል ጸለየች። ይህ ሞኝነት ይመስላል እንጂ፥ በዚህ ትምህርት የታወሩ ክርስቲያኖች ይህን የመሰለ ብዙ ሞኝ ልምምድ እንዳላቸው እንሰማለን። የዚህ ትምህርት ዋና አስተማሪ የሆነው ሰው "ከጌታ የሚፈልገውን ሁሉ ለመቀበል የሚያስችል አራት መመሪያ አለ" ይላል። ይኸውም፥ 1) "ይሆናል" በል፤ 2) አድርግ፤ 3) ተቀበል፤ 4) "እንደተቀበልክ ተናገር" የሚል ነው። በዚህ መንገድ ማንኛውም ሰው የትም ቢሆን የሚፈልገውን ሁሉ ሁልጊዜ ይቀበላል በማለት ያስተምራል። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እግዚአብሔር "የሚፈልጉትን ነገር የሚሰጥ ተላላኪያቸው" እንጂ "የሕይወታቸው ጌታ" አድርገው አይወስዱትም።

የዚህ እንግዳ ትምህርት መምህሮች ያዕቆብ 3፥6ን "ምላስ እንደ እሳት ናት፤ ምላስ በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፤ ሥጋችንንም ሁሉ ታረክሳለች፤ እንደ ገሃነመ እሳት ሰውነታችንን ታቃጥላለች" የሚለውን ጥቅስ ያለ አግባቡ ሲጠቀሙበት ይታያሉ። ያዕቆብ መጥፎ ምላስ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚያስከትለውን ጉዳት ለመግልጽ ነው። የዚህ የእንግዳ ትምህርት አስተማሪዎች ግን ከሥጋ ፈውስ ጋር ያያይዙታል። የታመመው ሰው "ያመኛል፣ ታምሜአለሁ" ብሎ ከተናገረ ልክ እንደተናገረው ይታመማል። "እንደ ንግግሩ ወይንም እንደ አባባሉ" እንዲሆንለት ከፈለገ ቢያመው እንኳ "አያመኝም ድኛለሁ" እያለ መመስከር አለበት ይላሉ። "ስለ በሽታ ካወራን በሽታን በራሳችን ላይ እናመጣለን" ይላሉ።

በነዚህ ነጥብ ላይ የነዚህ ሰዎች ትምህርት ከክርስቲያን ሳይንስ ትምህርትና እምነት ጋር በመጠኑም ቢሆን ይመሳሰላል። ክርስቲያን ሳይንስ ኃጢአት፣ በሽታ እንዲሁም ሞት መኖሩን ይክዳል። በዚህ ትምህርት አካባቢ ያሉ አንዳንድ አስተማሪዎች ይህን ያህል ይህን ትምህርት የሚያከሩ አይደሉም። ይኸውም፥ "ከታመማችሁ መታመማችሁን ታውቁታላችሁ፤ የተወናበዱ አንዳንድ ሰዎች ያንን መቀበል የለብኝም ይላሉ በመሠረቱ ከታመማችሁ ታማችኋል፣ ከተጎዳችሁ ተጎድታችኋል፣ የሚካድ ነገር አይደለም" ይላሉ። የዚህ ትምህርት አስተማሪዎች "ሆኖልኛል" ያላችሁት ነገር የተፈጸመም ባይሆንም በእምነት ዝም ብላችሁ "ተቀብያለሁ፣ የእኔ ነው በሉ"፤ ይሆንላችኋል ይላሉ። ይህን ትምህርታቸውን ብዙዎች ተለማምደውት በሕይወታቸው ብዙ ተአምር እንደሠራላቸው የሚጠቅሱት ታሪክ አላቸው። በሌላ አቅጣጫ ግን በዚህ ትምህርት ምክንያት ተወናብደው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች መኖራቸውን የሚያውቁ አይመስለኝም። ይህ እነዚህ አስተማሪዎች የሚያጠብቁት "እርግጠኛ የእምነት ኑዛዜ" (Positive Confession) ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው ልምምድ ሳይሆን እነርሱ የፈጠሩት የመበልጸጊያ አቋራጭ መንገድ ነው።

እምነት እንደ እግዚአብሔር ቃል እርሱን ለእኛ ግልጽ በአደረገው ጌታ መታመን ማለት ነው። በእውነት ላይ ያልተመሠረተ እምነት ደካማና እግዚአብሔርን ስለእርሱነቱ (ስለ አምላክነቱ) በመቀበል ፈንታ መጠቀምያ ብቻ ማድረግ ይሆናል። (Name it & Claim it) የእኔ ነው ብለህ ተቀበል በማለት እምነትን ሞኝነት ከሚያስመስሉ ልምምዶችና አስተማሪዎች እንጠንቀቅ። ይህን ዓይነቱ ትምህርት የብዙ ሰዎችን ስሜት ስለሚቀሰቅስ እንዲሁም የሰዎች ችግር "በገንዘብ በጤንነትና በሥራ" ላይ ያተኮረ በመሆኑ ይሄም ትምህርት ጫን የሚለው በነዚህ ላይ በመሆኑ በቀላሉ ብዙ ተከታዮችን ያስገኛል። በእውነት ላይ እንጂ እውነት በሚመስሉ ነገሮች ላይ መሠረታችንን አንመሥርት።

..............................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**